# <u>የሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ (CPO) ማረጋገጫ በርቀት ለሚገኝ ፍርድ ቤት</u>

*ይሄ ሰነድ የሚያወራው*

- ከፍርድ ቤት ችሎት ቀንዎ በፊት እንዴት መረጋጋት እንዳለብዎ (ገጽ 1)፣
- ከፍርድ ቤት ቀንዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ (ገጽ 2-3)፣ እና
- የፍርድ ቤት ቀንዎ ላይ ምን ማድረግ እንዳለብዎ (ገጽ 4-5)።

## <u>ራስዎን ይጠብቁ</u>

### ጊዜያዊ የጥበቃ ትዕዛዝ የወጣሎት ከሆነ፡-

- **የ TPO ኤልክትሮኒክ እና የታተመ ቅጂ ከእርስዎ ጋር ሁልጊዜ ያኑሩ።**
- **ተጨማሪ ቅጂዎችን ይያዙ።** የእርስዎ TPO "እንዳትጠጋ" ቦታዎች ውስጥ ያስቀምጧቸው (ልክ እንደ የስራ ቦታዎ፣ የቢሮ/የቤት አከራይዎ ጋር፣ ወይም የልጅዎ ትምህርት ቤት ወይም የሕፃናት ማቆያ)።

### ደህንነት የማይሰማዎት ከሆነ፡-

- ***ሕይወትዎ አደጋ ውስጥ እንደሆነ ሲሰማዎት ጊዜ በማንኛውም ሰዓት 911 ላይ ወዲያውኑ ይደውሉ።***
- ***አስቸኳይ የሆነ አደጋ ላይ ካልሆኑ፣ ሪፖርት ለማድረግ በአቅራቢያው የሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ ጋር ይደውሉ፡-***
    - ሌላኛው ወገን የ TPO ቅጂ ("በፍርድ ቤት ታዟል") ተሰጥቶታል ብለው የሚያስቡ ከሆነ፣ እና
    - የ TPO ን ትዕዛዝ እየጣሱ ነው ብለው የሚያምኑ ከሆነ።

*የቤት ውስጥ ጥቃት ክፍል ቢሮ (Domestic Violence Division Clerk's Office) በ (202) 879-0157፣ የ ዲሲ ሴፍን (D.C. SAFE) በ 1-844-443-5732 ስልክ ላይ መደወል፣ ወይም ጠበቃዎ ጋር በመደወል የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መዳፍር ክስ መመስረት ይችላሉ*

### ቤትዎን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ ቤት ማግኘት ላይ እገዛ ለማግኘት

- **የወንጀል ተጠቂዎች ካሳ (Crime Victims Compensation (CVC)) ክፍልን ያነጋግሩ።** ለሚከተሉት ነገሮች ለመክፈል ያግዞታል፡-
    - የበር ቁልፎችዎን መቀየር ወይም የውጭ መስኮትዎን ወይም መስታውቶን ማስተካከል፣ ወይም
    - በቤትዎ ውስጥ የደህንነት ስርዓት መግጠም፣ ወይም
    - የድንገተኛ ወይም ጊዜያዊ የመኖሪያ አማራጮችን ማግኘት፣ የሆነ ቦታ መንቀሳቀስ፣ ወይም ማግኘት ያልቻሉትን ደሞዝ ማካካስ።

*ከሶስቱ አንዱ መንገድ ላይ CVC ን ያግኙ፡-*

1. *CVC ጋር በ (202) 879-4219 ላይ ይደውሉ።*
2. *ኦንላይን እዚህ ላይ ያመልክቱ [https://www.dccourts.gov/services/crime-victims-compensation-matters/procedures](https://www.dccourts.gov/services/crime-victims-compensation-matters/procedures).*
3. *በአካል ወደዚህ አድራሻ ይሂዱ Moultrie Courthouse, 500 Indiana Ave NW Washington DC 20001 CVC የመጀመሪያው የሕንፃ ወለል መረጃ ዴስክ ላይ ይገኛል። የስራ ሰዓታቸው ሰኞ፣ እሮብ፣ እና አርብ ከጠዋቱ 9:00 am እስከ ከሰዓት 4:00 pm ድረስ ነው።*

***ጥያቄዎች?*** *(202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ [www.legalaiddc.org/online-intake/](www.legalaiddc.org/online-intake/)።*

**ከፍርድ ቤት ቀንዎ በፊት**

ከፍርድ ቤት ቀንዎ በፊት ሶስት ነገሮችን ማድረግ ይገባዎታል።

## እርምጃ ደረጃ 1፡- ክስ ሲሰማ እንደተዘጋጁ ያረጋግጡ።

- **ክስ የሚሰማበት ቦታ እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ መመሪያዎችን ለማግኘት ክስ ከሚሰማበት 2 ቀን በፊት ኢሜይልዎን ይመልከቱ።** ዳኛው ይሄንን መረጃ በኢሜይል ይልክሎታል እና ክስ ከመሰማቱ በፊት ይሄንን ኢሜይል ማንበብ አለብዎ።

- **በስልክዎ፣ ታብሌትዎ ወይም ኮምፒውተርዎ ላይ WebEx መተግበሪያን ይጫኑ።** የሚችሉ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በቪዲዮ ቢቀርቡ ይመርጣሉ። WebEx መተግበሪያ ክስ የሚሰማበት ቀን በቪዲዮ እንዲከታተሉ ያስችሎታል። እዚህ ላይ ያውርዱት፡- https://www.webex.com/downloads.html. መተግበሪያውን ማውረድ ካልቻሉ፣ በስልክ ክስ የሚሰማበት ቀን ላይ መደወል ይችላሉ።

- **ሙሉ ቀን ለመጠበቅ ይዘጋጁ።** ክስ የሚሰማበትን ሰዓት ምን ያህል እንደሆነ መወሰን ይከብዳል፣ እና ሙሉውን ቀን ሊወስድ ይችላል። ለረጅም ጊዜ ያህል መጠበቅ ሊያስፈልግዎ ይችላል። የሚችሉ ከሆነ፣ ከስራ ሙሉውን ቀን እረፍት ይውሰዱ።

## እርምጃ ደረጃ 2፡- ማስረጃዎን ያዘጋጁ።

- **Box.com ላይ ማስረጃዎን ይስቀሉ።** ይሄንን እንዴት ማድረግ እንደሚችሉ የሚነግርዎ አገናኝ ዳኛው ይልክሎታል። ከችሎቱ በፊት፣ ማስረጃዎን ይስቀሉ። ማስረጃው ሊያካትት የሚችለው፡-
  - የአካል ጉዳት ወም የንብረት መውደም የሚያሳዩ ፎቶዎች
  - የጽሁፍ መልዕክት ወይም የማህበራዊ ሚዲያ ቅጂዎች
  - የማንኛውም የንብረት መውደም ደረሰኞች
  - የሕክምና ማስረጃዎች እና ደረሰኞች
- **ምስክርዎ ክስ የሚሰማበት ቀን እንደሚገኝ ያረጋግጡ።** በተጨማሪ ማስረጃው የሚያካትተው የቃል ምስክርነት ነው(በመሃል ቃል መስጠት)። ምስክርዎ ዳኛውን ለማነጋገር ፍርድ ቤት መገኘት አለበት። ምስክርዎ የተፃፉ ጽሁፎችን ማቅረብ አለበት።

## እርምጃ ደረጃ 3፡- ተከሳሹ መጥሪያ እንደደረሰው ያረጋግጡ።

- **ተከሳሹ መጥሪያ እንደደረሰው እና እንዳልደረሰው ያረጋግጡ።**
  - *የዲሲ ፖሊስ ለተከሳሹ መጥሪያ እንዲሰጥልዎ የጠየቁ ከሆነ፡-* ፖሊስ መጥሪያውን እንዳደረሰ ለመጠየቅ የቤት ውስጥ ጥቃት ክፍልን (202) 879-0157 ላይ ይደውሉ።
  - *ተከሳሹ ከዲሲ ውጪ የሚኖር ከሆነ እና ፖሊስ መጥሪያ እንዲሰጥልዎ የጠየቁ ከሆነ፡-* ለተከሳሹ መጥሪያ እንደሰጡ ለመጠየቅ የአካባቢውን ፖሊስ ወይም ሸሪፍ መምሪያ ጋር ይደውሉ።
- **ፖሊስ ለተከሳሹ መጥሪያ ያልሰጠ ከሆነ፣ መጥሪያውን የሚሰጣቸው ሌላ ሰው ማግኘት ያስፈልጎታል።** ይሄንን እንዴት እንደሚያደርጉ መመሪያው ቀጣዩ ገጽ ላይ ይገኛል።

*__ጥያቄዎች?__ (202) 628-1161 ላይ ሊጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ www.legalaiddc.org/online-intake/።*

## *ያስታውሱ፡- ተከሳሹ መጥሪያ እንደደረሰው ያረጋግጡ!*

***መጥሪያ ምን ማለት ነው?***

- ለተከሳሹ *መጥሪያ* መስጠት ማለት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ደብዳቤ መስጠት ነው። ***ይሄንን በራስዎ ማድረግ አይችሉም—ወረቀቱን እንዲሰጥልዎ ሌላ ሰው ይጠይቁ።*** ከታች ይመልከቱ።

**ለተከሳሹ ማን *መጥሪያ* መስጠት ይችላል?**

- ***ማንኛውም አዋቂ ሰው*** ዕድሚያቸው 18 እና ከዛ በላይ የሆኑ ክሱ ላይ ምስክር ያልሆኑ ሰዎች ለተከሳሹ የፍርድ መጥሪያ ወረቀቱን እንዲሰጥሎት መጠየቅ ይችላሉ። በራስዎ መጥሪያውን እንዲሰጡ አይፈቀድሎትም።

- የሆነ ጊዜ ላይ ተካስሹ የት እንደሚገኝ የሚያውቁ ከሆነ፣ ለፖሊስ ደውለው እዚያ አካባቢ አቅራቢያ እንዲመጡ መጠየቅ ይችላሉ። ፖሊስ የፍርድ ቤት መጥሪያውን ይሰጣቸዋል። በእንደዚህ ዓይነት መንገድ መጥሪያውን ለፖሊስ ለመስጠት የመጥሪያውን ቅጂ ማምጣት አለብዎ።

**ለተከሳሹ *መጥሪያውን* ለመስጠት ምን ማሟላት ይጠበቅብኛል?**

- መጥሪያ እንደዚህ እንደተሰጠ ያረጋግጡ፡-

  (1) የ CPO ጥያቄ ያስገቡበት። *ይሄ ፍርድ ቤት የሞሉት ሰነድ ነው።*

  (2) ጊዜያዊ የጥበቃ ትዕዛዝ (ያለዎት ከሆነ)።

  (3) ክስ የሚሰማበት ማስታወቂያ እና ፍርድ ቤት የመገኘት ትዕዛዝ። *እነዚህ ፍርድ ቤቱ የሚልክልዎ ሰነዶች ናቸው።*

  (4) ማንኛውም ከፍርድ ቤት ጋር የሞሉት ሰነድ። *(ከአንድ በላይ ክስ የመሰረቱ ከሆነ።)*

**ሌላኛው ወገን *መጥሪያውን* አልቀበለም ያለ ከሆነስ?**

- መጥሪያውን የማይቀበሉ ከሆነ፣ መጥሪያውን የሚያደርስላቸው ሰው፡-
  - መጥሪያውን እግራቸው ላይ ሊያስቀምጥላቸው፣ **ወይም**
  - አብሯቸው ከሚኖር ሌላ አዋቂ ግለሰብ ሊሰጥ ይችላል።

**ተከሳሹ *መጥሪያ* እንደተሰጠው እንዴት *ማረጋገጥ* እችላለሁኝ?**

- መጀመሪያ፣ መጥሪያውን ለተከሳሹ የሚያደርሰው ግለሰብ ከሌሎች ወረቀቶች ጋር ለእርስዎ የሚላኩ "የመጥሪያ መመለስ" ቅጽ መሙላት አለበት። በተጨማሪም የዚህን ቅጽ ቅጂ እዚሀ ላይ ማግኘት ይችላሉ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/2019-07/Return%20of%20Service%20on%20Respondent.pdf.

- ክስ ከሚሰማበት ቀን በፊት ለመዝገብ ቤት ይሄንን ቅጽ ሞልተው ኢሜይል ማድረግ አለብዎ። ወደ dvd@dcsc.gov ይላኩት።

***ጥያቄዎች?*** *(202) 628-1161 ላይ ሊጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ www.legalaiddc.org/online-intake/።*

**<u>ክስ የሚሰማበት ቀን ላይ</u>**

## ቅደም ተከተል 1፡- የፍርድ ቤት መዝገብ ቤቱን ያግኙ።

- **ከጠዋቱ 8:30 am ላይ ያነጋግሩ።**
  - *ኦንላይን ለማነጋር፣ ወደዚህ ይሂዱ* https://dccourts.webex.com/meet/dvdhearings/.
  - *በስልክ ለማነጋገር፡-* የመዝገብ ቤቱን በ (202) 879-0157 ላይ ይደውሉ።
  - *የሚዘገዩ ከሆነ ወይም ኦንላይን ማገናኘት ካልቻሉ፡-* መዝገብ ቤቱ (202) 879-0157 ላይ ይደውሉ።
- **መዝገብ ቤቱን ያግኙ።**
  - ወደ እረፍት መውጫ ክፍል ይላካሉ። የመዝገብ ቤት ሰራተኛው ስምዎን እና የሚገኙበት መረጃ ይጠይቆታል።
  - ያዛኑ ቀን ቆየት ብሎ የፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ሰራተኛው አገናኝ ይልክሎታል።
- **በተጨማሪም በኢሜይልዎ ላይ የሚመዘገቡበትን መመሪያ ማየት እና ችግር ያጋጠሞት ከሆነ የዳኛውን ቻምበሮች በቀጥታ ደውለው ማግኘት ይችላሉ።**

## ቅደም ተከተል 2፡- ፍርድ ቤቱ ሲጠራዎት ጊዜ ዝግጁ እንደሆኑ ያረጋግጡ።

- **ፍርድ ቤቱ የሚጠራኝ መቼ ነው።**
  - በቀን ውስጥ በማንኛውም ሰዓት ሊጠራዎት ይችላል። ስልክዎ ቅርብ እንዳለ ያረጋግጡ።
- **የዘገየው ከሆነ ወይም ስልኩን መመለስ ካልቻልኩኝስ?**
  - ስልክ ጥሪ ያመለጥዎ ከሆነ፣ ለፍርድ ቤቱ መልሰው በፍጥነት ይመልሱ።
  - ፍርድ ቤቱ የክስ መዝገብዎ ሊሰርዝ ይችላል። የክስ መዝገብዎ የተሰረዘ ከሆነ፣ 2 አማራጮች አሎት፡-

    (1) ክስ በድጋሚ እንዲታይ ለፍርድ ቤቱ ድጋሚ ክስ መመስረት። በክስ መስማት ሂደቱ ላይ ለምን እንዳልተገኙ ይግለጹ።

    (2) አዲስ ክስተቶች ለወደፊቱ የተፈጠሩ ከሆነ አዲስ CPO ጥያቄ ያስገቡ።

## ተከሳሹ የማይገኝ ከሆነ ምን ማድረግ አለብኝ?

| ተከሳሹ ***መጥሪያ ካልተሰጠው*** እና ክስ ሲሰማ ያልተገኘ ከሆነ፡- | ተከሳሹ ***መጥሪያ የተሰጠው*** እና ክስ ሲሰማ ያልተገኘ ከሆነ፡- |
|---|---|
| **ለተከሳሹ መጥሪያውን ለመስጠት ለዳኛው ተጨማሪ ጊዜ ይጠይቁ።** የ "2 ሳምንት ጊዜ" እንዲሰጥዎ እንደሚፈልጉ ይግለጹ።<br><br>*TPO ያለዎት ከሆነ፡-* ወደ ፍርድ ቤት ተመልሰው እስከሚመጡ ድረስ TPO እንዲራዘም ለዳኛው ይጠይቁ። | **"ማቅረብ አልተቻለም" በማለት ለዳኛው ይጠይቁ** ይሄ ምንም እንኳን ተከሳሹ ክስ ሲሰማ ባይገኝም ዳኛው የጥበቃ ትዕዛዝ ሊሰጥዎት ይችላል ማለት ነው።<br><br>ለዳኛው ምን እንደተፈጠረ ይንገሯቸው እና ማስረጃዎን ያሳዩዋቸው። *የበለጠ ለማወቅ ቀጣዩ ገጽ ላይ ይመልከቱ።* |

***ጥያቄዎች?*** *(202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ* www.legalaiddc.org/online-intake/።

## ክስ ከመሰማቱ በፊት ስምምነት ማድረግ፡-

- *እርስዎ እና ተከሳሹ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ተመዝግባችሁ ሳለ፡-*
    - ለፍርድ ቤቱ የሚሰራ አቃቤ ሕግ አደራዳሪ ይደውልሎታል።
    - በሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝዎ (CPO) ውስጥ ምን እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው።
    - ተከሳሹን የሚጠይቁት ነገር ላይ እንደሚስማሙ ይጠይቋቸዋል።
    - የአቃቤ ሕግ አደራዳሪው ከአንድ ጊዜ በላይ ሊደውልሎት ይችላል።
    - ተከሳሹን ማናገር የለብዎትም።
- *ተከሳሹ ያቀረቡት ጥያቄ ላይ የሚስማማ ከሆነ፡-* ክስ የሚሰማበት ቦታ ላይ፣ ዳኛው CPO ን ይመለከታል እና ሁሉቱም ወገኖች እንደተስማሙ ለማረጋገጥ ይሞክራል። ተከሳሹ ኦንላይን ትዕዛዙ ላይ ይፈርማል።
- *ተከሳሹ ያቀረቡት ጥያቄ ላይ የማይስማማ ከሆነ፡-* ክሱ ሲሰማ ጊዜ፣ ሁለቱም ወገኖች ማስረጃቸውን ያቀርባሉ።

## ክስ በሚሰማበት ሰዓት፡- ምን እንደተከሰተ ይግለጹ፡- ማስረጃዎን ያቅርቡ።

- ያቀረቡት ክስ ላይ ለዳኛው የእያንዳንዱን ክስተት ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ ይናገሩ።
- ከተከሳሹ ጋር ያለዎትን ግንኙነት ይግለጹ።
- Box.com ላይ የሰቀሉትን ማንኛውም ማስረጃ ያስረዱ።
- ተከሳሹ ሊጠይቅዎ የሚችሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይዘጋጁ።
- ምስክርዎ ክስ የሚሰማባት ቦታ ላይ እንዲገኝ ያድርጉ እና ለዳኛው እንዲናገሩ ያድርጉ። *የተከሳሹ ወገን እነሱንም ጥያቄ ሊጠይቃቸው እንደሚችል እንደሚያውቁ ያረጋግጡ።*
- ተከሳሹ እና የእነሱ ምስክሮች ምን እንደሚሉ ያድምጡ። ያሎትን ማንኛውም ጥያቄዎች ይጠይቋቸው።

## ክስ በሚሰማበት ሰዓት፡- ዳኛው CPO የፈረደልዎ ከሆነ ምን ማድረግ ይጠበቅቦታል።

- **CPO የተሰጥዎ ከሆነ፣ ለዳኛው የሚፈልጉትን ጥበቃ ዓይነት መጠየቅ ይችላሉ።** CPO እስከ ሁለት ዓመት ድረስ እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ። ለዳኛው እነዚህን ለመናገር ይዘጋጁ፡-
    - ተከሳሹ በቀጥታም ሆነ በሶስተኛ ወገን በኩል እንዳያገኝዎ የሚፈልጉ ከሆነ።
    - ተከሳሹ ከእርስዎ፣ ከተወሰነ ቦታ ወይም ከተወሰኑ የእርስዎ ሰዎች እንዲርቅ የሚፈልጉ ከሆነ።
    - ተከሳሹ ለጠፋው ንብረት ወይም የሕክምና ወጪ ካሳ እንዲከፍሉ የሚፈልጉ ከሆነ።
    - ከቤትዎ ተከሳሹ ዕቃቸውን ሲወስዱ ወይም ለቀው ሲወጡ፣ ወይም ከቤታቸው ውስጥ እርስዎ ዕቃዎን ሲያወጡ፣ ፖሊስ እንዲገኝልዎ የሚፈልጉ ከሆነ።
    - የምክር አገልግሎት ላይ ተከሳሹ እንዲገባ ፍርድ ቤቱ እንዲያዝ የሚፈልጉ ከሆነ።